# የወላጆችና የትምህርት ቤት ግንኙነት:- መኃፖ ላ ፔትተ

ማረው ዓለሙ*

*አህጽሮተ ጥናት፤ የጥናቱ አቢይ ዓላማ በወላጆችና በትምህርት ቤቶች መካከል ያለውን ግንኙነት መመርመር ነው:: ተጠኝዎቹ በባህርዳር ከተማ* በ1992 ዓ.ም. በ12 *አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ* 211 *መምህራንና በነዚሁ ትምህርት ቤቶች የምትማር/የሚማር ቢያንስ አንዲት/አንድ ልጅ ያላቸው* በ17*ቱ ቀበሌዎች ነዋሪ ሆነው መምህር ያልሆኑ* 211 *ወላጆች ናቸው:: በመጠይቅ አማካይነት ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መጣኝና ገላጭ መረጃዎች ተሰብስበዋል:: በመረጃው ትንተና መሠረትም በወላጆችና በመምህራን መካከል ስለሚኖር ግንኙነትና በትምህርት ቤት የወላጆችን ተሣትፎ በተመለከተ በወላጆችና በመምህራን መካከል በጥቅሉ በስታትስቲክስ የጐላ* (P>0.05) *የግምት ልዩነት አለመኖሩ ታይቷል:: ይህን ውጤት ግን ገላጭ መረጃው በተወሰነ መልኩም ቢሆን ድጋፍ አልሰጠውም:: በትምህርት ቤት ተሣትፎ እንዲያደርጉ በሚጠሩበት ጊዜ ብዙ ወላጆች እምቢተኞች ስለመሆናቸው መምህራኑ በአብዛኛው ይስማማሉ:: በተናጠል በተደረገው ትንተና ግን በወላጆችና በመምህራን መካከል ስለሚኖር ግንኙነት ሁለቱም አዎንታዊ ግምት አላቸው:: በተጨማሪም የወላጆችና የመምህራን ግንኙነት አስፈላጊ ስለመሆኑ ሁለቱም የሚጋሯቸው የስምምነት ነጥቦች አሏቸው:: በትምህርት ቤት የወላጆችን ተሣትፎ በተመለከተ ግን በወላጆችና በመምህራን መካከል በስታትስቲክስ አስተማማኝ* (P<0.05) *ልዩነት ተገኝቷል:: ከገላጭ መረጃው በተገኘው ውጤት መሠረት የወላጆች ተሣትፎ አስፈላጊ ስለመሆኑ ሁለቱም የሚስማሙባቸው ነጥቦች ቢኖሩም፣ ተሣትፎው በራሳቸው በወላጆች አዎንታዊ ግምት ሲኖረው፣ በመምህራን ግን አሉታዊ ግምት ነው ያለው:: ጥያቄ በጥያቄ ከተደረገው ትንተና ለመረዳት እንደተቻለው አዎንታዊ የሚመስለው የወላጆች ግምት ቢሆንም፣ በብዙ ጥያቄዎች ዝቅተኛ ውጤት የተመዘገበበት ስለሆነ ወላጆች ለተሣትፏቸው ሙሉ ድጋፍ አላቸው ለማለት አያስደፍርም:: ስለዚህም በፍላጐት ብቻ የተወሰነ የሚመስለውን የወላጆችና የትምህርት ቤቶች ግንኙነት ወደ ተግባር ማሸጋገር ያስፈልጋል::*

## *መግቢያ*

በፔምህርፔ ዙሪሽ ጸሚተረ ፟ፔ ምርምሮኖ አትቱ በወላ ኖ በፔምህርፔ ቤፔ መካጸል ሽለውት ትባፉትፔ ባሚመለጸፔ ትው:: በመስጹ ጸሚተረ ፟ፔ ባምርምር ውጎ ኖም ፔምህርፔ ቤ ኖ፣ መምህራት ወላ ኖ ተጎቃሚ ሽሆ ሉ:: በአትኃ ወሽም በሌላ መልክ በተለሽብ ፟ዜሽፔ ባሚተረ ፟ፔ ምርምሮኖ በአጎቃላሽ ፔምህርፔት በማሻሻል ረ ታ ባባራሳ ው አስተዋኾ ትተሚ ራ ው

---

* ረ ፔ ዞ ሮወሰር - ባህር ር ብኚሽርሲቲ

መ መፔ አቨስ ርም፡፡ ፝ ብት ባበለነ ለመረ ፔ ት ፞ኖልም በመስጹ ባተተረሰባ ውት ትዛቤዎኖ ነ ኖ መቃገፎ ቭነ ቅማል፡፡

ፋራንት (1980) እንደሚያስረዱት፣ ዘልማዳዊ በሆነው አሠራር የትምህርት ሥራ የወላጆችን ጣልቃ ገብነት አይፈልግም፡፡ በርካታ ትምህርት ቤቶችም ወላጆችን ከማቅረብ ይልቅ፣ ማግለልን ይመርጣሉ፡፡ በዚህም የተነሣ ትምህርት ቤቶች የወላጆችን ተሣትፎ ለማጐልበት የሚያደርጉት ጥረት በጣም ትንሽ የሚባል መሆኑን በሬስ (1996) ያስገነዝባሉ፡፡ ወላጆች ልጆቻቸውን ወደትምህርት ቤት ከላኩ በኋላ ሙሉውን ኃላፊነት የሚሠጡት ለመምህራን ነው፡፡ ሆኖም ኤቢይ (1997) እንደሚያስረዱት፣ ወላጆች ልጆቻቸውን ወደትምህርት ቤት በሚልኩበት ጊዜ ብዙ ተስፋዎችና ምኞቶች አሏቸው፡፡ ትምህርት ቤቶች ለልጆቻቸው ትምህርት የተመቻቸ ሁኔታ እንዲፈጥሩ ይፈልጋሉ፤ ልጆቻቸው በትምህርታቸው ልቀው እንዲከበሩና አድናቆትን እንዲያገኙ ይሻሉ፡፡ ይህ የተለያየ ምኞትና ፍላጐት እውን እንዲሆን ግን የእነሱን ተሣትፎ የሚጠይቅ ስለመሆኑ ግንዛቤው የላቸውም፡፡ መምህራንም ቢሆኑ ሥራችንን/ሥልጣናችንን ይጋፋሉ በሚል እምነት ከወላጆች ጣልቃ ገብነት ነፃ ሆነው መሥራትን እንደሚመርጡ በጆንሰን (1995) የተጠቀሰው የዋረን (1988) ጥናት አመላክቷል፡፡ ይህ ጥናት የወላጆችና የመምህራን ግንኙነት መሠረት እንደሌለው ከማሳየቱም በተጨማሪ፣ የወላጆች ተሣትፎ በመምህራንም ሆነ በራሣቸው በወላጆች ላይ ከፍተኛ ያለመረጋጋት እንደሚፈጥር አረጋግጧል፡፡ ብላሴና ጆሴፍ ብላሴ (1997) እንደሚያስረዱትም በትምህርት ቤት የወላጆችን ተሣትፎ በተመለከተ መምህራንና ወላጆች ራሣቸው ግምታቸው/እይታቸው (views) ይለያያል፡፡ የወላጆች ተሣትፎ ውጤት ያለው ስለመሆኑ መምህራን ምንጊዜም ቢሆን ጥርጣሬ አላቸው፡፡ ወላጆችም ቢሆኑ ራሳቸውን ከመምህራን በታች ዝቅ አድርገው ስለሚያዩ በትምህርት ቤት ውሳኔዎች ላይ ነፃ ሆነው አይሳተፉም፡፡ ቭህም ለሁለቱም ባ ራ ፝ ቭ በሆቿው በፔምህርፔ ስራ ላቭ ባ ራ ትዛቤ አለመ ሩት ሸመላክ ል፡፡

ዘመናዊ በሆነው አስተሳሰብ ግን በጣም አስፈላጊና ጠቃሚ የተባለው የትምህርት ተሐድሶ እንቅስቃሴ በትምህርት ቤቶችና በወላጆች መካከል ትብብራዊ ሥራን ማጠናከር እንደሆነ ሁለት ጸሀፍት (ፖሎዋይና ፖቶን 1997) ያስረዳሉ፡፡ የጋራ ትብብሩ የመማር ማስተማሩን ሥራ ውጤታማ እንደሚያደርገው ለማንም የተሰወረ አይደለም፡፡ እንደነጃሮሊሜክና ፎስተር (1997) አገላለጽም፣ ወላጆችና መምህራን የጋራ ዓላማና ግብ ስላላቸው፣ በተለይም ወላጆች ስለልጆቻቸው ትምህርት ከመምህራን የበለጠ ኃላፊነት ስላለባቸው፣ ከመምህራን ጋር መመካከር እንዲችሉ፣ መምህራን ሁልጊዜ

በራቸውን ክፍት ሊሸተር፦ ብ ባል:: የትምህርቱ ሥራ ትርጉም የሚ ረው ለውጤትም የሚበቃው የወላጆች ድጋፍ ሲጨመርበት እንደሆነ፣ ወላጆችና መምህራን የጋራ ግንዛቤ ሊኖራቸው ይገባል::

ወላጆች የመማር ማስተማሩን ሂደት ዳረኛ ሆኖ ከማየት፣ ውስጎ ገብተው አቢይ ሚና ሊጫወቱ ይገባል:: እንደበሬስ (1996) አገላለጽ፣ በተለይም የዘመኑ የትምህርት ሥራ ውጤታማነት የሚወሰነው በወላጆች ተሳትፎ ነው:: በመሆኑም በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት ልጆቻቸው የሚማሩባቸውን ትምህርት ቤቶች ጐብኝተው የማያውቁ ወላጆች ጉዳይ በዘመኑ ከፍተኛ ትኩረት የሚሻ መሆኑን ፖይኔና ሂንዲስ (1986) የጠቀሷቸው ባርከር ሉን (1970)፣ ስይስተርና ክሊፍት (1980) እና ኃይልስቶኔ (1984) ያስረዳሉ:: በትምህርት ቤት የወላጆች ተሳትፎ በተማሪዎች የትምህርት ውጤት ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ እንዳለው የተለየዩ የምርምር ውጎቶች በዋቢነት ይጠቀሣሉ:: ሂንዶርሰንን (1987) ጠቅሰው ማኮምብስ ውሂስለር (1997) እንደሚያስረዱት፣ የወላጆች ተሳትፎ የተማሪዎችን ውጤት በከፍተኛ ደረጃ ያሻሽላል:: ተመሳሳይ የትምህርት ደረጃና ዳራ ካላቸው ተማሪዎች መካከል፣ ወላጆቻቸው በትምህርት ቤት ተሳትፎ ያላቸው ተማሪዎች፣ ወላጆቻቸው ተሳትፎ ከማያደርጉ የላቀ የትምህርት ውጤት እንዳስመዘገቡ የሄንዶርሰን ጥናት አረጋግጧል:: በትምህርት አመቱ መጨረሻ ላይ ከክፍል ወደክፍል ያልተዛወሩ ተማሪዎች ሳይቀሩ በትምህርት ቤት የወላጆቻቸውን ድጋፍ በማግኘታቸው በአስገራሚ ሁኔታ ከፍተኛ ለውጥና መሻሻል እንደታየባቸው ይኸው ጥናት አረጋግጧል:: በተጨማሪም በትምህርት ቤት የወላጆች ተሣትፎ ተማሪዎች ለሚማሩባቸው ትምህርት ቤቶች አዎንታዊ ግምት እንዲኖራቸውና የተሻለ የመማር ፍላጐትም እንዲያጐለብቱ እንዳስቻላቸው ጥናቱ አሣይቷል:: በብላሴና ጆሴፍ ብላሴ (1997) የተጠቀሰው የካሜር (1984) ጥናትም የወላጆች ንቁ ተሳትፎ በትምህርት ቤት ውስጥ ትርጉም ያለው ማህበራዊና ትምህርታዊ ለውጥ እንደሚያመጣ በተመሣሣይ ሁኔታ አረጋግጧል:: በ ር ጎ በመምህራት ጎ ረፔ ላብ ባወላ ኖ ተሳፔ0 ሲ መርበፔ በፔምህርቱ ላብ መሻሻል ሊ ር ስለሚኖል ባጎ ቷ ውጎፔ ባሚሸስተትቅ ላብሆት ብኖላል::

በመሆኑም ጃሮሊሜክና ፎስተር (1997) እንደሚያስረዱት፣ በተለይም በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የወላጆች ተሳትፎ አስፈላጊነት በአስገራሚ ሁኔታ እያደገና እየጐለበተ መጥቷል:: እንደክሊክ (1981) አገላለጽ፣ በትምህርት ቤት ውስጥ ወላጆች በብዙ መንገድ ሊሳተፉ ይችላሉ:: በዕቅድ አወጣጥ፣ በድጋፍ ሰጭነት፣ በመማሪያ ማስተማሪያ ክፍል ውስጥ ሳይቀር ለመምህራን እገዛ በማድረግ ወይም ልጆቻቸውን በቤት አካባቢ እንዴት መርዳት እንዳለባቸው

በመሰልጠን ከሚሳተፉባቸው መካከል ጥቂቶቹ ናቸው። በተመሳሳይ ሁኔታ ጃሮሊሜክና ፎስተር (1997) ወላጆች በትምህርት ቤት እቅድ አወጣጥ ላይ ውሳኔ በመስጠትና አስተዳደራዊ ድጋፍ በማድረግ፣ ሥርዓተ ትምህርቱን በማጐልበትና ልጆቻቸውን በትምህርታቸው በማገዝ ሊሳተፉ እንደሚችሉ ያስረዳሉ። ስለዚህም የትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎች የመማር ማስተማሩን ሥራ ለማጐልበት የወላጆችን እውቀት፣ ክሂልና ልምድ ከመጠቀም ወደኋላ ማለት እንደሌለባቸው አጋርዋል (1981) ያስገነዝባሉ። የህክምና ባለሙያ ወላጆች ለምሳሌ ስለጤና አጠባበቅና ልዩ ልዩ የሰውነት አካላት እንዴት እንደሚሰሩ እንዲያስተምሩ ሊጋበዙ ይችላሉ። በሌሎች መስኮች እውቀት፣ ክሂልና ልምድ ያላቸው ወላጆችም በተመሳሳይ ሁኔታ በየሙያቸው የሚኖራቸው አስተዋጽኦ ከግምት መግባት ይኖርበታል።

አጋርዋል (1981) እንደሚያስረዱት፣ ወላጆችና መምህራን በመተባበር ከሰሩ ሁለቱም በጋራ ተጠቃሚዎች ናቸው። ከመምህራን አንፃር ለምሣሌ የሚከተሉት ይጠቀሣሉ።

- ከወላጆቻቸው በርካታ መረጃዎችን ለማግኘትና ከዚሁ አንፃር ተማሪዎቻቸውን ሙሉ በሙሉ ለማወቅ ይችላሉ፣
- ስለተማሪዎች የእለት ተእለት የትምህርት ሁኔታ ከወላጆች የሚፈለገውን ድጋፍ ያገኛሉ፣
- ከመማሪያ ክፍል ውጭ እንዲሰሯቸው ለተማሪዎች የሚሰጡ የቤት ሥራዎች በወላጆች እንዲታገዙ ያደርጋሉ፣
- ለትምህርት ቤት የገንዘብና የሌላም ቁሳቁስ ድጋፍ ለማግኘት ይችላሉ፣
- የተለያዩ እቅዶችን ተግባራዊ ለማድረግና ጥቅም ላይ ለማዋል ይችላሉ፣

ከወላጆች አንፃር ደግሞ ቀጥሎ ያሉት ጠቀሜታዎች ይጠቀሳሉ።

- ስለልጆቻቸው የትምህርት ሁኔታ የተሻለ መረጃ ያገኛሉ፣
- ለመፃህፍትና ለሌሎች የትምህርት መሣሪያዎች ምን ያህል ወጭ መመደብ እንዳለባቸው በቀላሉ ያውቃሉ፣
- በልጆቻቸው ላይ ችግሮች ከመድረሳቸው በፊት አስቀድመው ምንጫቸውን በማወቅ መከላከል ይችላሉ፣
- ትምህርት ቤቶች ለልጆቻቸው የሚሠጧቸውን የቤት ሥራዎች ተገቢነትና ትክክለኛነት ለመገምገም ይችላሉ፣

- ልጆቻቸው ለሚማሩባቸው ትምህርት ቤቶች ምን ዓይነት ድጋፍ መስጠት እንዳለባቸው ይገነዘባሉ፣

በዚህም መሠረት ጆንሰን (1995) እንደሚያስገነዝቡት፣ ወላጆች በቤትና በትምህርት ቤት ላለው አስፈላጊ ግንኙነት መሠረት መሆናቸውን መምህራን መገንዘብ አለባቸው፡፡ ጠቃሚ የመረጃ ምንጮቻቸው መሆናቸውን ከግምት በማስገባት ወላጆች ጠንካራ ተሳትፎ እንዲኖራቸው መምህራን ሊያበረታቷቸው ይገባል፡፡ ተማሪዎቻቸው በሚታመሙበት ጊዜ ለምሣሌ መምህራን ከቤታቸው ድረስ ሂደው ቢጠይቋቸው የወላጆች የትምህርት ቤት ፍቅር እንደሚጨምር አጋርዋል (1981) ያስገነዝባሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ እንደጉድ ብሮዋ (1997) አገላለጽ፣ ወላጆች ስለልጆቻቸው አስፈላጊ መረጃ እንዲሰጡ ወደትምህርት ቤት እንዲመጡ በሚጠሩበት ጊዜ መምህራን አስቀድመው ስለልጆቻቸው የሚያውቁትንና በትክክል የተገነዘቡትን በግልጽ ሊነግሯቸው ይገባል፡፡ ከወላጆችም ተጨማሪ አስተያየት በመጠየቅ ስለተማሪዎች የተሻለ መረጃና ግንዛቤ ማግኘት ይቻላል፡፡

ኤቢይ (1997) እንደሚያስረዱት ደግሞ፣ መምህራን ስለትምህርቱ ዓላማ፣ ስለተማሪዎች የመማር ሁኔታና የትምህርት እድገት ለወላጆች በየጊዜው ሪፖርት በማድረግ ግንኙነታቸውን ማጠናከር ይችላሉ፡፡ በዚህ መልኩ የወላጆችን የትምህርት ቤቱን ዓላማ የማገዝና የማጐልበት ፍላጐት መጨመር ይቻላል፡፡ የሁለትዮሽ ግንኙነት ጠንካራ ከሆነም የተማሪዎች በራስ የመተማመን ችሎታ ያድጋል፡፡ የፑምፍሬይ (1986) ጥናት እንዳረጋገጠው የወላጆችና የትምህርት ቤት ግንኙነት መጠናከር በማንኛውም መልኩ የተማሪዎችን ትምህርት በማጐልበት ረገድ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

ለማጠቃለል የዘመኑ የመማር ማስተማር ሂደት የወላጆችን ተሳትፎ የግድ አድርጐታል፡፡ ወላጆች ከመምህራን የበለጠ ስለልጆቻቸው ትምህርት ሃላፊነት ስላለባቸው፣ ስለልጆቻቸው የተለየ ፍላጐት፣ ምኞትና ችሎታ የሚሰጧቸው መረጃዎች የመማር ማስተማሩን ሥራ በከፍተኛ ደረጃ ያጠናክረዋል፡፡ በመሆኑም በትምህርቱ ሥራ ተሣትፎ እንዲኖራቸው የሚበረታቱ ከሆነና ልጆቻቸው ለተሻለ ውጤት የሚበቁባቸውን ብልሃቶች ከተገነዘቡ በቤትና በትምህርት ቤት ጠንካራ መሠረት ያለው ግንኙነት ለመመሥረት ይችላሉ (ጆንሰን 1995)፡፡ ይሁን እንጂ አንዳቸው ከሌላቸው ምን እንደሚጠብቁ ወይም የአንዳቸው ሥራ በሌላቸው እንዴት መታገዝ እንዳለበት ወይም የአንዳቸው ሚና ለሌላቸው ሥራ አስፈላጊነቱ ምን ያህል እንደሆነ በግልጽ አለመረዳት በወላጆችና በመምህራን መካከል ጠንካራ የመተጋገዝ ግንኙነት አለመኖር ዋና

ምክንያት መሆኑን የፓይኔና የሂንዲስ (1986) ጥናት አረጋግጧል፡፡ ግንዛቤ በሌለበት ግንኙነትን ማጠናከር ስለማይቻል የጥናቱ ውጤት ምክንያታዊ ይመስላል፡፡

እነዚህን መሰል ጥናቶችና ከላይ በክለሣው የተጠቀሱት ድርሳናት የውጩን አገር ልምድና ችግር መሠረት አድርገው የቀረቡ ናቸው፡፡ በኢትዮጵያም ባወላ ኖት ባፔምህርፔ ቤ ኖት ትዤቾፔ በተመለጾተ በጎ ቱ ባለቤፔ አቅም ውስትችፔ ባተሟሉ ሊሆት ባቫኖሉም፣ አት ትፇ ፇርሳ ፔት በማኃቀሰ ለመ ም ም ተሞክሯል፡፡ አ ሱት ባፔምህርፔ ባስልጎ ዝሊሲ ባፔምህርፔ ሴክተር ስፔራ (1994$_a$፣ 1994$_b$)፣ ሀብ ሙት (1994)፣ ብኤስኤአቫ /ኢፔቮእቨት (1993) ት ሁም ፔምህርፔ ሚኒስ ርት (1993) ዋቢ በማፇረ ሀብ ሙ (2001) ትተሚቨስረቱፔ ጾሽ ሩ መት ስፔ በዋፔ በቒረው ባፔምህርፔ ስርዓፔ፣ በዝሊሲ ቀረኟ ሆት በአጎ ቃላቫ በፔምህርፔ ሥራ ረ ፇ ባወላ ኖ፣ ባመምህራት ባህብረተሰቡ ተሳፔዐ በኃም ውስት ቒር፡፡ በተር መውተቅ ማ ስፔ በተመሠረተው ባሽ ር መት ሥፔ ባተቀረ ው ባፔምህርፔ ሥልጎ ዝሊሲ (1994) ት በመማር ማስተማሩ ባህብረተሰብት ተሳፔዐ ቫወቅ ል፡፡ በዚሁ ዝሊሲ ቅፇሚቨ ፔጹረፔ ጾተሰኃ ው ብኖ አትተቾውም ባፔምህርፔ አመራርት አተረ ፔት መለወኅ ቲው፡፡ በዚህም መሠረፔ ለምሳሌ ባፔምህርፔ ቤ ኖ ባፔምህርፔ አመራር አተረ ፔ ባልተማጾለ መልጹ ጾህብረተሰቡ፣ ጾሚመለጾ ው ባልማፔ ባምርምር ተቋሞኖ፣ ጾመምህራት ጾተማሪዎኖ በተወኃጎ ቦር ኖ ወቨም ኮሚ ዎኖ ቫዋቀራል፡፡ ባፔምህርፔ ሴክተር ስፔራ (1994) ፇርሳት በተመሳሳቫ ሁቴ ትተሚቨሳባውም በህብረተሰቡ በፔምህርፔ ቤ ኖ መካጾል ቨለው ትዤቾፔ ጎትካራ መሠረፔ ት ረው ቫጎበቃል፡፡ ባአካባቢው ህብረተሰብ ለፔምህርፔ ቤ ኖ ተህትቾፔ መሻሻል ላዋቾፔ ት ወስፇ ቫተረ ል፡፡

ሆ ም ባፔምህርፔ አመራር አተረ ፔ፣ ባህብረተሰብ ተሳፔዐ ባዌቫ ትስ መመሪቨ (1994) ትተሚቨመላክተው ዝሊሲውት መሠረፔ በማፇረ በመ መሪቨ፣ ፔምህርፔት በተመለጾተ ህብረተሰቡት ቨሳተዊ ባፔምህርፔ ቤፔ ኮሚ ዎኖ ባወረ ሥልጎ አመራር ቦር ኖ ባተቋቋሙ ቢሆትም ውጎ ማ ሊሆት ት አልኖሉም፡፡ በመሆት በዚህ ረ ፇ ባተጾሰቱፔት ኖ ሮኖ ለማቃለል በፔምህርፔ ቤፔ ተረ ባወላ መምህር ህብረፔ፣ በቀበሌ በወረ ተረ ባቀበሌ ባወረ ፔምህርፔ ሥልጎ አመራር ቦር ኖ ጾህብረተሰቡ ተወኃጎተው ትተ ተዋቅረዋል፡፡ ሀብ ሙ (2001) በፔምህርፔ ሥራ ባማህበረሰብ ማለፔም ባወላ ኖ፣ ባመምህራት፣ ባተማሪዎኖ አ ባብቾፔ ቨላ ው አካላፔ ተሳፔዐ መጎ ጾር ት ለበፔ በማውሳፔ፣ ጾወላ ኖ፣ ጾመምህራት ጾማህበረሰብ አባላፔ ባተውኃጎ ባፔምህርፔ ቤፔ ኮሚ ዎኖ በብዙ ፔምህርፔ ቤ ኖ መመስረ ውት ቨስረ ሉ፡፡ ቫሁት ት በአ ስ

አበባ በሌሎና ክልሎና ትተሚስተዋለው፣ ለፔምህርፔ ቤ ኖ ቢ በማሰባሰብ፣ መምህራትት በመ ም ም አመ ዊ ሪዠር ኖት በማ መጎ ብኖ ሳብወሰት ወሳፖ በሆት ባአካ ሚክ ባአስተ ተር ተ ባራፔ ላብም ባመወሰት ሥልኃት ለዋትቱ ሊ ራ ው ትተሚ ባ ተመራማሪው ጎቁመዋል::

ጸላብ ለማሳባፔ ትተተሞጸረው አሁት ባለው ሁት ባፔምህርፔ ዠሊሲው ባህብረተሰቡት ተሳፔዐ ባሚጎብቅ ባሚሽበረ ቢሆትም ውጎ, ማትቱት ለመ ም ም ብሎም ፔምህርፔት ለማሻሻል ት ባተመራማሪዎኖት ፔጹረፔ ሊሽ ፖ ባሚ ባ ብመስላል:: ለዚህም ነው በትምህርት ሚኒስቴር በህዝብ ግንኙነት ክፍል በሚታተመው ***መጽሔተ ትምህርት*** ከተጠቀሱት የትምህርት ጥናት የትኩረት አርዕስፔ **የወላጆችና የትምህርት ቤቶች ግንኙነት** አትተኞው ሆ ባቀረበው:: ብህም ለዚህ ጎ ፔ ዋፔ ሰጎ ል:: በመሆኑም ጥናቱ በወላጆችና በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (ከአንደኛ ክፍል እስከ ስድስተኛ ክፍል ያሉትን ብመለጸ ል) መካከል ያለውን ግንኙነት ይመረምራል:: ለዚህ ጥናት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተመረጡበትም ዋናው ምክንያት በዚህ ደረጃ ያሉት ተማሪዎች በአካልም ሆነ በአእምሮ ያልበሰሉ በለጋ እድሜ ላይ የሚገኙ በመሆናቸው፣ ስለትምህርታቸው ሙሉ ኃላፊነት መሸከም ስለሚሳናቸው ከሌሎች በተለየ የወላጆች ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው መሆኑን በማመን ነው:: በዚህም መሠረት ጥናቱ ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄዎች የመመለስ አላማ አለው::

- በመምህራንና በወላጆች መካከል ያለው ግንኙነት አዎንታዊ/አሉታዊ ነውን?
- ወላጆች በትምህርት ቤቶች ስለሚኖራቸው ተሳትፎ የመምህራን ግምት/እይታ ምን ይመስላል?
- ወላጆች በትምህርት ቤቶች ስለሚኖራቸው ተሳትፎ የራሳቸው ግምት ምንድን ነው?
- በወላጆችና በትምህርት ቤቶች መካከል ስለሚኖር የጋራ መተጋገዝ አብሮ የመሥራት ግንኙነት እንቅፋት የሆኑ ችግሮች ምንድን ናቸው?

## 2. ባመሰረ ዊ ቃላፔ ኽከሰ-ሀሳቡኖ አጎ ቃቀም (operational definition)

- **ትፑቶፔ**:- በጎ ቱ ባቃሉ አጎ ቃቀም ለ ራ አላማ (ለፔምህርፔ ስራ) አብሮ በመተ ዝ መስራፔ ወብም መተሳሰብ ማለፔ ነው፤

- **ባአን ት ዘቲ:-** በተን ሯዎኖ አመራረኅ፣ በመረ መሰብሰቢሽ መሳሪሽ ዝ ፔ፣ በመረ አሰባሰብ፣ አተ ተት አተረቿም ኅ ቱ ባተጾተለውት ባአሰራር ስልፔ ሽሳሽል፤
- **መኃሯ (quantitative):-** በኅ ቱ ባተሰበሰቡፔት መረ ዎኖ ዓብችፔ አተ ተት ባሚመለጸፔ ሲሆት፣ በመረ ዓብችፔ አሀዛዊ መ ለ ሽላ ውት ሊቆንሩ ሊሰሉ ባሚኖሉፔት ሲወክል፣ በአተ ተት ረ ታ ተ ሞ አ ባብ በሆቅ ባስ ፔስቲክስ ቀመሮኖ መተትተት ሽለምትም አታልዎ ተ ባ ውኀ፣ፔ ላብ መታረስት ሽሳሽል፤
- **ላ (qualitative):-** በአሀዝ ባማብ ለኽ መረ ዎኖት ብወክላል:: በኅ ቱ ተን ሯዎኖ በመንብቁ በክዎፔ ለቀረበው ኅሽቄ ባሰኃ ውት ችኻ ሀሳቦኖ አስተሽባ ኖ ብመለጸ ል:: ቕዚህ መረ ዎኖ ተቆንረው በአሀዝ ተሰልተው ባሚተቅተት ሳብሆቅ ቅተባተዛም ው ተተራ ተው በቃላፔ ባሚ ለኽ በመሆ ው ባቃሉ አን ቃቀም ባመራ ዎቷት አተ ተትም ብ ምራል፤
- **ላ ቅፖ ዊ:-** በመንብቅ አማካብችፔ ባተን ሯዎኖት አስተሽባፔ ወብም አመለካጸፔ በመቃዧፔ መ ለ ወብም ፔትተ በማታረ ወተማን ቃለሽ መታረስ ማለፔ ቕው፤
- **ምክችሽ ዊ ሙ** (purposive sampling):- ተን ሯዎኖ ለኅ ቱ ጾሚወለ ው መረ ር ጾሌሎኖ በተለባ መልጹ ቅርብ አስወላ ሆቕው በመ ዧ ው ሆት ተብሎ ባተመረን መሆ ውት ሽሳሽል፤

## የአጠናን ዘዴ

ጥናቱ አላማውን ከግብ ለማድረስ የተከተለው የአጠናን ስልት ገላጭ ቅኝታዊ (descriptive - survey study) የምርምር ዘዴን ሲሆን፣ በቅኝት የተገኙትን መረጃዎች በመተንተን ይገልፃል፣ የተደረሰበትን ማጠቃለያም ያቀርባል::

## ተጠኝዎች

በባህር ዳር ከተማ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራንና በነዚህ ትምህርት ቤቶኖ የምትማር/የሚማር ቢያንስ አንዲት/አንድ ልጅ ያላቸው መምህር ያልሆኑ ወላጆች ወብም አሳ ዎኖ የዚህ ጥናት ተጠኝዎች ናቸው:: በባህር ዳር ከተማ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት የሚሰጥባቸው

የመንግሥት ትምህርት ቤቶች 12 ሲሆኑ፣ በነዚህ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ 211 መምህራን ሁሉም በተጠኝነት ተመርጠዋል:: ሆኖም የትምህርት ቤቶቹ ስፋትና ጥበት ተመሳሳይ ባለመሆኑ የሁሉም ትምህርት ቤቶች የተጠኝ ብዛት ተመጣጣኝ አይደለም:: ሠንጠረዥ 1 በትምህርት ቤት የተጠኝዎችን ብዛት ያሳያል::

**ሠንጠረዥ 1፡ የተጠኝዎች ብዛት በትምህርት ቤት**

| ተ.ቁ | የት/ቤት ስም | የተጠኝ ብዛት | ተ.ቁ | የት/ቤት ስም | የተጠኝ ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሠርፀ ድንግል | 15 | 7 | ድልችቦ | 15 |
| 2 | ፋሲሎ | 16 | 8 | ፀሐይግባት | 15 |
| 3 | እውቀት ፋና | 15 | 9. | መስከረም 16 | 17 |
| 4 | ሽንብጥ | 21 | 10. | ፈለገ አባይ | 19 |
| 5 | ጠይማ | 22 | 11. | መጋቢት 28 | 16 |
| 6 | ቁልቋል ሜዳ | 23 | 12. | ሹም አቦ | 17 |
| | | ጠቅላላ ድምር | | 211 | |

በተመሳሳይ ሁኔታ በባህር ዳር ከተማ በ17ቱ ቀበሌዎች ነዋሪ የሆኑ 211 ወላጆች በምክትሽፔ ሙና (purposive sampling ) አማካይነት በጥናቱ ተካትተዋል:: ሽህም ባሆቱፔ ምክትሽፔ ለጎ ቱ ጾሚወለ ው መረ ር ጾሌሎኖ በተለባ ቅርብ ሆትው ( ወላ ኖ ለጎ ቱ በተመረጎ፟ፔ ፔምህርፔ ቤ ኖ ቢሽትስ አትቃ/አት ፟ፔ ል ሽላ ው መምህር ሽልሆት፣ መምህራት ለጎ ቱ በተመረጎ፟ፔ ፔምህርፔ ቤ ኖ ባሚሽስተምሩ በመሆ ው) በመ ዡ ው ትው:: በየቀበሌው የተመረጡት ተጠኝዎች ብዛት ከሞላ ጐደል ተመሳሳይ (በአብዛኛው በአንድ ቀበሌ 12) ሲሆን፣ በቀበሌ 03፣ 07፣ 09፣ 13፣ 15፣ 16፣ 17 ግን በእያንዳንዱ ቀበሌ 13 ተጠኝዎች ተካትተዋል:: ተጠኝዎቹ ባተመረጎ፟ፔ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ትምህርት ፋኩልቲ በቢዝነስ ትምህርት ክፍል በ1992 ዓ.ም. በማታው ፕሮግራም የምርምርና የሪፖርት አፃፃፍ የተሰኘውን ኮርስ በአጥኚው በሚማሩ 350 ተማሪዎች አማካይነት ነው:: ተማሪዎቹ በሚኖሩባቸው ቀበሌዎች በመንግሥት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የምትማር/የሚማር ቢያንስ አንዲት/አንድ ልጅ ያሏቸውና መምህር ያልሆኑ ወላጆችን መዝግበው እንዲያመጡ በማድረግ ለሚፈለገው መረጃ አግባብነት ያላቸው ተጠኝዎች በምክትሽፔ ባ ሙ ዘዴ ተመርጠዋል::

## *የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ*

የጥናቱን ዓላማ መሠረት በማድረግ መረጃ እንዲያስገኝ የተመረጠው የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ የጽሑፍ መጠይቅ ነው። መጠይቁ በወላጆችና በትምህርት ቤቶች መካከል ያሉትን ልዩ ልዩ መስተጋብሮች እንዲያሳይ በሚል አላማ ተዘጋጅቷል። በመጠይቁ መጣኝ (quantitative) መረጃ እንዲያስገኙ 30 ጥያቄዎች ተካትተዋል። ከነዚህም መካከል 15ቱ (2፣ 4፣ 5፣ 7፣ 8፣ 10፣ 11፣ 13፣ 16፣ 20፣ 21፣ 23፣ 26፣ 27፣ 29) የወላጆችንና የመምህራንን ግንኙነት በተመለከተ አንጻቸው ስለሌላቸው ያላቸውን ግምት የሚለኩ ሲሆኑ፣ 15ቱ ደግሞ (1፣ 3፣ 6፣ 9፣ 12፣ 14፣ 15፣ 17፣ 18፣ 19፣ 22፣ 24፣ 25፣ 28፣ 30) በትምህርት ቤቶች የወላጆችን ተሳትፎ በተመለከተ ራሳቸው ወላጆችና መምህራን ምን ዓይነት ግምት እንዳላቸው እንዲለኩ የተዘጋጁ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ ተጠኝዎቹ የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን በተመለከተ ግላዊ አስተያየታቸውን እንዲያሰፍሩ የሚጋብዝና ገላጭ (qualitative) መረጃ የሚያስገኝ አንድ ነፃ ጥያቄ ቀርቧል። የዚህ ጥያቄ ዓላማ የወላጆችን በትምህርት ቤት የመሳተፍ ፍላጐትና በዚህም ረገድ የመምህራንን አዎንታዊ/አሉታዊ ግምት በተዘዋዋሪ መለካት ነው።

በመጠይቁ ከ30ዎቹ ጥያቄዎች መካከል የተወሰኑት ፓይኔና ሂንዲስ (1986) የወላጆችንና የመምህራንን ግንኙነት ለማጥናት ካዘጋጇቸው ጥያቄዎች አስፈላጊው ለውጥና ማሻሻያ ተደርጐባቸው ለዚህ ጥናት እንዲስማሙ ሆነው በውርስ የተወሰዱ ሲሆኑ፣ ቀሪዎቹ ደግሞ ጥናቱን በተመለከተ የተነበቡ ተዛማጅ ድርሳናትን መሠረት በማድረግ በአጥኚው የተዘጋጁ ናቸው።

በመጠይቁ የእያንዳንዱ ጥያቄ ምላሽ የሚወሰነው በአራት ነጥብ መልስ መስጫዎች (scales) ነው። አማራጮችም ከከፍተኛ ወደዝቅተኛ በጣም ስማማለሁ (4)፣ እስማማለሁ (3) አልስማማም (2) እና በጣም አልስማማም (1) የሚሉ የመልስ መወሰኛ ነጥቦችን ይዘዋል። አማራጭ የመልስ መወሰኛ ነጥቡ በዚህ ቅደም ተከተል መሠረት ተግባራዊ የሚደረገው በአዎንታ ለቀረቡት ጥያቄዎች ሲሆን፣ በአሉታ ለቀረቡት ግን (3፣ 4፣ 5፣ 8፣ 9፣ 10፣ 12፣ 13፣ 21፣ 26) ነጥቡ የሚመዘገብላቸው በተገላቢጦሽ ነው። ተጠኝዎች ለምሣሌ ለ10ኛው ጥያቄ የመረጡት 4ን ቢሆን በተገላቢጦሽ የሚመዘገብላቸው ነጥብ 1 ነው።

ከላይ ለማሳየት እንደተሞከረው መጠይቁ ከሌላ ተመሳሳይ ጥናት በውርስና ከተዛማጅ ድርሣናት በአጥኚው ከተዘጋጀ በኋላ በሁለት ባለሙያዎች

ተገምግሟል። የተሰጡ የማሻሻያ አስተያየቶችንም መሠረት በማድረግ ለመጨረሻ ጊዜ በአጥኚው ተዘጋጅቷል። ከዚያም በተጠኝዎች ልክ ተባዝቶ ለመምህራን በ12 ትምህርት ቤቶች ርእስ መምህራን፣ ለወላጆች ደግሞ በመረጧቸው የአጥኚው ተማሪዎች አማካይነት በሚያዝያ ወር 1992 ዓ.ም. ታድሎ ከአንድ ሳምንት በኋላ ተሞልቶ ተመልሷል።

የጥናቱ መረጃ ተሰብስቦ አስፈላጊው ቆጠራና የማደራጀት ሥራ ከተሠራ በኋላ በመጀመሪያ የመጠይቁ አስተማማኝነት በ 'Cronbach alpha' ከተለያየ አቅጣጫ ተሰልቷል። በዚህም መሠረት የመጠይቁ አጠቃላይ አስተማማኝነት $\alpha = 0.725$ ሲሆን፣ ለመምህራን $\alpha = 0.740$ እና ለወላጆች $\alpha = 0.713$ አስተማማኝነት ተመዝግቦበታል። በሌላ በኩል ደግሞ በወላጆችና በመምህራን መካከል ስለሚኖር ግንኙነት የሁለቱን ግምት ለመለካት የተዘጋጁት 15 ጥያቄዎች አጠ ቃላይ አስተማማኝነት $\alpha = 0.579$ ሲሆን፣ እነዚሁ ጥያቄዎች ለመምህራን ብቻ $\alpha = 0.598$ አስተማማኝነት ሲያስመዘግቡ ፣ ለወላጆች ብቻ ደግሞ $\alpha = 0.559$ አስመዝግበዋል። እንዲሁም በትምህርት ቤት የወላጆችን ተሳትፎ በተመለከተ የወላጆችንና የመምህራን ግምት ለመለካት የተዘጋጁት 15 ጥያቄዎች አጠቃላይ አስተማማኝነት $\alpha = 0.579$ ሲሆን፣ እነዚሁ ጥያቄዎች ለወላጆች ብቻ $\alpha = 0.592$፣ ለመምህራን ደግሞ 0.559 አስተማማኝነት አሳይተዋል። ሁሉም ውጤቶች የመጠይቁን አስተማማኝነት ያሳያሉ።

## የመረጃ አተናተን ዘዴ

መጠይቁን መሠረት በማድረግ አስፈላጊው መረጃ ከተሰበሰበ በኋላ የመረጃዎቹ አጠቃላይና ተናጠላዊ ንጽጽር በ 'two - tailed t - test' ተሰልቷል። ይህም የመምህራንንና የወላጆችን የአመለካከት ልዩነት ለመፈተሽ የሚያገለግል ሲሆን ገላጭ መረጃውን ለመተንተን ግን ገላጭ ትንተና ተግባራዊ ተደርጓል።

## 4. የጥናቱ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ

በዚህ ክፍል የጥናቱ ውጤት ትንተና ማብራሪያ በቅደም ተከተል ይቀርባል።

### የጥናቱ ውጤት ትንተና

በወላጆችና በትምህርት ቤት መካከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ በመምህራንና በራሳቸው በወላጆች ያለውን አዎንታዊ/አሉታዊ ግምት

ለመለካት በአንድ በኩል ከመምህራንና ከወላጆች ግንኙነት፣ በሌላ በኩል ደግሞ በትምህርት ቤት ከወላጆች ተሳትፎ አንፃር ለማየት የተሞከረ ቢሆንም በሠንጠረዥ 2 እንደተመለከተው በመጀመሪያ ጥቅል መረጃውን ነው ለመተንተን የተሞከረው፡፡

**ሠንጠረዥ 2፡ ስለወላጆችና መምህራን ግንኙነትና ስለወላጆች የትምህርት ቤት ተሳትፎ የወላጆችና የመምህራ ግምት (views) አጠ ቃላይ ንጽጽር**

| ወላጆች n = 211 | | መምህራን n = 211 | | t - test |
|---|---|---|---|---|
| $\bar{x}$ | sd | $\bar{x}$ | sd | |
| 92.635 | 7.712 | 92.251 | 7.868 | -0.506* |

*P >0.05 df = 420

ሠንጠረዥ 2 እንደሚያሳየው የወላጆች አማካይ ውጤት 92.635 ሲሆን፣ የመምህራን 92.251 ነው፡፡ በሁለቱ ውጤቶች መካከል የጐላ ልዩነት የሚታይ አይመስልም፡፡ የልዩነቱ አለመጉላትም በስታትስቲክስ አስተማማኝነቱ ተረጋግጧል፡፡ ለምናልባት ስህተት 5% በመተው በተሠራው ስሌት በአጠቃላይ ንጽጽር በወላጆችና በመመህራን መካከል ላለው ግንኙነትና ወላጆች በትምህርት ቤት ስለሚኖራቸው ተሳትፎ፣ በመምህራንና በወላጆች መካከል የግምት ልዩነት አለመኖር በስታትስቲክስ የጐላ ልዩነት (P>0.05) አለመሆኑን ሠንጠ ረዡ ያሳያል፡፡ በተጨማሪም በወላጆችም ሆነ በመምህራን መካከል ያለው የግምት ልዩነት ወጥነት (consistency) ያለው መሆኑን የመደበኛ ልይይት (sd) ውጤቶቻቸው ያመላክታል፡፡ የወላጆች መደበኛ ልይይት 7.712 ሲሆን፣ የመምህራን 7.868 ነው፡፡ በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት ከግምት የሚገባ ካለመሆኑ በተጨማሪ ተጠያቂዎቹ ለእያንዳንዱ ጥያቄ የሰጡት ምላሽ አንደኛው ከሌላኛው ወጥነት ያለው መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

በሠንጠረዥ 2 የቀረበው መረጃ አጠቃላይ ንጽጽር ያስገኘው ውጤት ተናጠላዊ በሆነ ትንተና ሲታይ ተመሳሳይ ውጤት ስለማሳየት አለማሳየቱም ለማየት ተሞክሯል፡፡ በሠንጠረዥ 3 እንደተመለከተው የወላጆች አማካይ ውጤት 45.199 ሲሆን፣ የመምህራን 45.730 ነው፡፡ ልዩነታቸው ከግምት የሚገባ አይደለም፡፡ የስታትስቲክስ ውጤቱም ይህንኑ ያረጋግጣል፡፡

**ሠንጠረዥ 3፡ በወላጆችና በመምህራን መካከል ስለሚኖር ግንኙነት የወላጆችና የመምህራን ግምት ንጽጽር**

| ወላጆች n = 211 | | መምህራን n = 211 | | |
|---|---|---|---|---|
| $\bar{x}$ | sd | $\bar{x}$ | sd | t - test |
| 45.199 | 4.413 | 45.730 | 4.364 | 1.242* |

*P >0.05 df = 420

በወላጆችና በመምህራን መካከል ስለሚኖር ግንኙነት፣ በወላጆችና በመምህራን መካከል የግምት ተዛምዶ መኖሩንና ይህም በስታትስቲክስ አስተማማኝ (P>0.05) አለመሆኑን ሠንጠረዥ 3 ያሣያል። የመደበኛ ልይይት ውጤታቸውም ይህን የሚያጠናክረው ይመስላል። የወላጆች መደበኛ ልይይት 4.413 ሲሆን፣ የመምህራን 4.364 ነው። ይህም በሁለቱ መካከል ከግምት የሚገባ ልዩነት አለመኖሩን ከማሳየቱም በተጨማሪ የውጤቶቹ ዝቅተኛነትም የተጠያቂዎቹን የአመላለስ ወጥነት (consistency) ያመለክታል።

በመጠይቁ የተገኘው ገላጭ (qualitative) መረጃ ግን ይህን ውጤት አይደግፈውም። ወላጆች ከመምህራን ጋር የመመካከር ልምድ እንደሌላቸውና ስለልጆቻቸው የትምህርት ድክመትም ሆነ የተለየ ፀባይ ማሳየት ለመመካከር ወደትምህርት ቤት በሚጠሩበት ጊዜ እምቢተኞች መሆናቸውን በርካታ መምህራን ይስማማሉ። በግንኙነቱ አስፈላጊነት ላይ ግን መምህራኑም ሆኑ ወላጆች ቀጥሎ ከተጠቀሱት ነጥቦች አንፃር የጋራ ስምምነት እንዳላቸው ከሁለቱም የተገኙት ምላሾች ያረጋግጣሉ። እንደአብነትም ከተሰጡት ምላሾች የሚከተሉት ይገኙባቸዋል።

- ለትምህርት ጥራት የወላጆች፣ የመምህራንና የመንግሥት የተቀናጀ ሥራ ያስፈልጋል፤
- ወላጆችና መምህራን በተወሰነ ጊዜ እየተገናኙ መመካከር አለባቸው፣
- ወላጆችንና መምህራንን የሚያቀራርብ ዘዴ መቀየስ አለበት፤
- በተለይም ተማሪዎቻቸው በትምህርታቸው ድክመት ወይም የተለየ ፀባይ ሲታይባቸው መምህራን ሳይዘገዩ ወላጆቻቸውን ማማከር አለባቸው፤
- ወላጆችና መምህራን በየጊዜው በደብዳቤ የሚገናኙበት መንገድ መመቻቸት አለበት፤

- ተማሪዎች በትምህርት ድክመት ወይም የተለየ ፀባይ ሲያሳዩ ብቻ ሳይሆን፣ ወላጆችና መምህራን በማንኛውም ጊዜ እየተገናኙ ስለተማሪዎች ትምህርት ጠንካራና ደካማ ጐኖች ቢመካከሩ ጥሩ ነው፤
- ወላጆች፣ መምህራንና ተማሪዎች በአንድ ላይ ተገናኝተው የሚመካከሩበት ልምድ ቢመጣ ጥሩ ነው፣
- ወላጆቸ ስለልጆቻቸው ልዩ ልዩ ችግሮች ከመምህራን ጋር ቢመካከሩ አስፈላጊውን እገዛ ለማድረግ ያስችላቸዋል፤

በትምህርት ቤት የወላጆችን ተሣትፎ በተመለከተ በወላጆችና በመምህራን መካከል ያለው የግምት ንጽጽርም እንዲሁ ራሱን ችሎ ታይቷል፡፡ ውጤቱ ግን በሠንጠረዥ 2 እና 3 ከተገኘው ጋር ተደጋጋፊነት አላሣየም፡፡ ሠንጠረዥ 4 እንደሚያሳየው የወላጆች አማካይ ውጤት 47.436 ሲሆን፣ የመምህራን ደግሞ 46.521 ነው፡፡ በሁለቱ መካከል ልዩነት ያለ ይመስላል፡፡ ይህም ልዩነት በስታትስቲክስ ተረጋግጧል፡፡

ሠንጠረዥ 4፡ በትምህርት ቤት የወላጆችን ተሳትፎ በተመለከተ የወላጆችና የመምህራን ግምት ንጽጽር

| ወላጆች n = 211 | | መምህራን n = 211 | | t - test |
|---|---|---|---|---|
| $\bar{x}$ | sd | $\bar{x}$ | sd | |
| 47.436 | 4.381 | 46.584 | 4.537 | -2.107* |

*P < 0.05 df = 420

በሠንጠረዥ 4 የሁለቱን አማካይ ውጤቶች (47.436 እና 46.584) መነሻ በማድረግ ለመረዳት እንደሚቻለው በትምህርት ቤት የወላጆች ተሳትፎ ከመምህራን ይልቅ በራሣቸው በወላጆች ድጋፍ ያለው ይመስላል፡፡ መምህራን ግን የወላጆችን ያህል ጠንካራ ድጋፍ የሠጡት አይመስልም፡፡ ከገላጭ (qualitative) መረጃ የተገኘው ውጤት ግን የዚህ ተቃራኒ ነው፡፡ በትምህርት ቤት የወላጆችን ተሳትፎ በተመለከተ ወላጆችና መምህራን በአስፈላጊነቱ ከሚከተሉት ነጥቦች አንፃር ይስማማሉ፡፡

- የተማሪዎችን የዲሲፕሊን ችግር ለመፍታት የወላጆች ተሳትፎ በጣም ያስፈልጋል፤

- ተማሪዎች ወላጅ አምጡ ሲባሉ ወላጆቻቸውን በመፍራት ወላጅ ያልሆኑ ሰዎችን ያመጣሉ፤ ይህን ችግር ለመፍታት የወላጆች የትምህርት ቤት ተሳትፎ ወሳኝ ነው፣
- ወላጆችና ትምህርት ቤቶች እጅና ጓንት ሆነው ካልሠሩ የመማር ማስተማሩ ሂደት በግማሹ ነው የሚካሄደው፤
- ወላጆች ልጆቻቸውን በትምህርት ቤት የመጐብኘት ግዴታ እንዳለባቸው የሚደነግግ ደንብ መውጣት አለበት፣
- ወላጆች ተጠርተው ሳይሆን፣ ራሣቸው አስበው ወደ ትምህርት ቤት የመምጣትና ልጆቻቸውን የመጐብኘትና የመከታተል ግዴታ አለባቸው፤
- ወላጆች ከትምህርት ቤቶች ጋር እየተመካከሩ በተለያዩ ሥራዎች (ለምሣሌ ወንበር በመጠገን፣ አጥር በማጠር፣ ተጨማሪ የመማሪያ ክፍሎችን በመስራት/በመጠገን ወዘተ.) መሣተፍ አለባቸው፣

በተጨማሪም በትምህርት ቤቶች ባሉ ችግሮች ዙሪያ ቀጥሎ ያሉት የወላጆችና የመምህራን የጋራ አስተያየቶች ተመዝግበዋል፡፡

- ከልጆች እድሜ ጋር የተጣጣመ ትምህርት ይሰጥ፤
- የሚሠጠው ትምህርት በጣም ከባድ በመሆኑ ተማሪዎች ከወላጆቻቸው ጠይቀው ለመረዳት አይችሉም፣
- ከማንኛውም ሃይማኖት ነፃ የሆነ የግብረገብ ትምህርት እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት መሰጠት አለበት፣
- ሳይታመሙ ፈቃድ የሚጠይቁ ተማሪዎች መታመማቸው ሳይረጋገጥ ስለሚፈቀድላቸው አልባሌ ቦታ እየዋሉ ናቸው፣
- በኮሚቴ ስብሰባና በሌሎች ድርጅታዊ ሥራዎች ምክንያት በትምህርት ሥራ አዘውትረው የማይገኙ መምህራን አሉ፤
- የመምህራን ምክርና ግሣፄ በብዙ ተማሪዎች ዘንድ ዋጋ እያጣ ነው፣
- ተማሪዎች በትምህርት አቀባበላቸውም ሆነ በፀባያቸው ብዙ ችግሮች አሉባቸው፤

ከነዚህ ነጥቦች መረዳት እንደሚቻለው መምህራንም ሆኑ ወላጆች ራሳቸው ከሚያደርጓቸው ይልቅ እንዲደረጉላቸው የሚፈልጓቸው ጉዳዮች ብልጫ ያላቸው ይመስላል፡፡ በተለይም ወላጆች ኤቢይ (1997) እንደሚያስረዱትም፣ ልጆቻቸውን ወደትምህርት ቤት ሲልኩ ከብዙ ምኞትና ፍላጐት ጋር በመሆኑ አስተያየታቸው ብዙም የሚያስደንቅ አይሆንም፡፡

ከላይ ከሠንጠረዥ 2 እስከ ሠንጠረዥ 4 ለተገኘው ጥቅል ውጤት በመጠይቁ የተካተቱት የግምት መለኪያ ጥያቄዎች በተናጠል የራሣቸው የሆነ አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ተጽእኖ እንዳላቸውና እንደሌላቸው በዝርዝር ማየቱ አስፈላጊ ስለሚሆን፣ ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ በእያንዳንዱ ጥያቄ ላይ ትንተና ይደረጋል፡፡

በሠንጠረዥ 3 እንደተመለከተው በወላጆችና በመምህራን መካከል ስለሚኖር ግንኙነት በመምህራንና በወላጆች መካከል ያለው የግምት ልዩነት በስታትስቲክስ (P>0.05) የጐላ አይደለም፡፡ ነገር ግን ይህን ተዛምዶ ለመለካት የቀረቡት 15 ጥያቄዎች ለውጤቱ እኩል አዎንታዊ አስተዋጽኦ እንደሌላቸው ሠንጠረዥ 5 ያሳያል፡፡

**ሠዥጠረዥ 5፡ በወላጆችና በመምህራን መካከል ስለሚኖር ግንኙነት የወላጆችና የመምህራን ግምት ጥያቄ በጥያቄ ንጽጽር**

| ጥያቄዎች | ወላጆች n = 211 $\bar{x}$ | ወላጆች sd | መምህራን n = 211 $\bar{x}$ | መምህራን sd | t - test |
|---|---|---|---|---|---|
| ብዙ ወላጆች የመምህር ሥራ እውቀት ማስተላለፍ እንደሆነ አድርገው ይቆጥራሉ፡፡ | 3.223 | 0.835 | 3.313 | 0.855 | 1.09** |
| መምህራን ስለሚያስተምሯቸው ተማሪዎች ብዙ እውቀት ባይኖራቸው ይመረጣል፡፡ | 3.720 | 0.554 | 3.687 | 0.586 | -0.608** |
| ወላጆች ልጆቻቸውን ከሚያስተምሩ መምህራን ጋር ለመወያየት ሲፈልጉ፣ አስቀድመው ቀጠሮ ሊይዙ ይገባል፡፡ | 3.137 | 0.831 | 3.161 | 0.863 | 0.287** |
| ወላጆች ልጆቻቸውን የሚያስተምሩ መምህራንን እንዲያውቋቸው ያስፈልጋል፡፡ | 3.341 | 0.723 | 3.479 | 0.664 | 2.035* |
| ተማሪዎች ከት/ቤት ውጭ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች በተመለከተ ወላጆቻቸውን ማማከር የመምህራን የሥራ ድርሻ አይደለም | 3.081 | 0.899 | 3.100 | 0.853 | 0.222** |
| ወላጆች የት/ቤቱን በር አልፈው ወደ ግቢ ባይገቡ ለመምህራን ጥሩ ነው | 3.540 | 0.670 | 3.465 | 0.664 | -1.168** |
| ርእሰ መምህራን በተቻላቸው ሁሉ የብዙ ተማሪዎችን ወላጆች እንዲያውቋቸው ያስፈልጋል | 2.972 | 0.823 | 2.981 | 0.900 | 0.113** |
| ወላጆች በጉርብትና አብረዋቸው የሚኖሩ መምህራንን በጥላቻ አይን የማየት አዝማሚያ ይታይባቸዋል | 3.299 | 0.757 | 3.147 | 0.678 | -2.169* |
| ወላጆች ልጆቻቸውን በትምህርት ላይ እንዳሉ እንዲጐበኟቸው ት/ቤቶች የጉብኝት ቀን ቢኖራቸው ይመረጣል | 3.137 | 0.772 | 3.043 | 0.739 | -1.289** |
| ወላጆች ወደ ት/ቤት ሲመጡ ከቤታቸው ያሉ ያህል እንዲሠማቸው መምህራን አስፈላጊ ሁኔታዎችን ማመቻቸት አለባቸው | 3.094 | 0.775 | 3.057 | 0.785 | -0.499** |
| ወላ ኖ የተማሪዎችን ችግር በተመለከተ ከመምህራን ጋር የሚያደርጉት መመካከር ምንጊዜም ቢሆን ከት/ቤት ውጭ መካሄድ የለበትም | 2.810 | 0.901 | 2.706 | 0.946 | -1.160** |
| መምህራን ተማሪዎቻቸው በሚታመሙበት ጊዜ ከቤታቸው ድረስ ሂደው ቢጠይቋቸው፣ የወላጆች የት/ቤት ፍቅር ይጨምራል | 3.251 | 0.761 | 3.111 | 0.775 | -3.233* |
| ልጆቻቸው በት/ቤት ውስጥ ችግር ካላጋጠማቸው በስተቀር ወላጆች ከመምህራን ጋር እንዲገናኙ አያስፈልግም | 3.284 | 0.720 | 3.194 | 0.721 | -1.284** |
| ተማሪዎች በት/ቤት ውስጥ እያሉ ከባድ ችግር ቢያጋጥማቸው ከቤታቸው ድረስ ሂደው ለመጠየቅ መምህራን ዝግጁ መሆን አለባቸው | 3.038 | 0.742 | 2.839 | 0.776 | -2.692* |
| ወላጆች በልጆቻቸው ላይ ስለሚደርስ ከባድ ችግር ከመኖሪያ ቤታቸው ድረስ በመሄድ ከመምህራን ጋር መመካከር አለባቸው | 2.507 | 0.891 | 2.341 | 0.866 | -1.939** |

* P<0.05 **P>0.05 df = 420

ሠንጠረዥ 5 እንደሚያሳየው ለ15ቱ ጥያቄዎች ወላጆችና መምህራን ሙሉ በሙሉ ተመሳሳይ ግምት የላቸውም። ለምሳሌ ወላጆች ልጆቻቸውን የሚያስተምሩ መምህራንን እንዲያውቋቸው አስፈላጊ መሆኑ በመምህራን ድጋፍ ሲኖረው፣ በወላጆች ግን ድጋፍ አላገኘም። ወላጆች መምህራኑን ባያውቃቸው የሚመርጡ ይመስላል። በተቃራኒው ደግሞ መምህራን ተማሪዎቻቸው ችግር ባጋጠማቸው ጊዜ ከቤታቸው ድረስ ሂደው ለመጐብኘት አለመፈለግን ሲመርጡ፣ ወላጆች ግን ድጋፍ አላቸው። ልዩነቱ በስታትስቲክስም አስተማማኝ (P<0.05) መሆኑን ሠንጠረዡ ያሳያል። የወላጆች ተጐራባች መምህራንን በጥላቻ ዓይን የማየት አዝማሚያም ሌላው አስተማማኝ ልዩነት የታየበት ጥያቄ ነው። ሀሳቡን ወላጆች ራሣቸው የሚስማሙበት ሲሆን፣ መምህራኑ ግን የሚቃወሙት ይመስላል።

በአጠቃላይ በጥያቄ 7፣ 13፣ 23፣ 27 ላይ በወላጆችና በመምህራን መካከል በስታትስቲክስ አስተማማኝ (P<0.05) የግምት ልዩነት መኖሩንና በቀሪዎቹ ሌሎች ጥያቄዎች ላይ ግን የጐላ ልዩነት (P>0.05) አለመኖሩን ሠንጠረዥ 5 ያመለክታል።

በትምህርት ቤት የወላጆችን ተሳትፎ በተመለከተም በቀረቡት 15 ጥያቄዎች ላይ የወላጆችና የመምህራን ግምት ጥያቄ በጥያቄ ተነፃጽሯል። በሠንጠረዥ 6 እንደተመለከተው በብዙዎቹ ጥያቄዎች ላይ ወላጆችና መምህራን ተመሳሳይ ግምት ሲኖራቸው በ5 ጥያቄዎች (1፣ 3፣ 6፣ 17፣ 30) ላይ ግን ባ ላ (P<0.05) የግምት ልዩነት አላቸው። በነዚህ ጥያቄዎች መሠረት ደግሞ በትምህርት ቤት የወላጆች ተሣትፎ በአብዛኛው በመምህራን ድጋፍ ሲኖረው፣ በወላጆች ግን ድጋፍ ያለው አይመስልም።

## ሠንጠረዥ 6፡ በትምህርት ቤት የወላጆችን ተሳትፎ በተመለከተ የመምህራንና የወላጆች ግምት ጥያቄ በጥያቄ ንጽጽር፣

| ጥያቄዎች | ወላጆች n = 211 | | መምህራን n = 211 | | t - test |
|---|---|---|---|---|---|
| | $\bar{x}$ | sd | $\bar{x}$ | sd | |
| ወላጆች ት/ቤቶችን በሙያቸው እንዲያግዙ መበረታታት አለባቸው | 3.555 | 0.640 | 3.720 | 0.519 | 2.924* |
| ስለልጆቻቸው የትምህርት ሁኔታ የፈተና ወረቀቶቻቸውን በማየት ማወቅ ስለሚችሉ ወላጆች ለዚሁ ብለው ወደ ት/ቤት መሄድ የለባቸውም | 3.246 | 0.820 | 3.450 | 0.763 | 2.643* |
| ወላጆች የት/ቤቱን ግቢ በማስዋብ ሥራ ሊሣተፉ ይገባል | 2.827 | 0.827 | 3.175 | 0.751 | 3.944* |
| በአጠቃላይ አነጋገር ልጆቻቸው የተሻለ የትምህርት ተሣትፎ እንዲኖራቸው መርዳት እንዳለባቸው ብዙ ወላጆች ግንዛቤ የላቸውም ለማለት ይቻላል:: | 1.981 | 0.822 | 2.123 | 0.902 | 1.692** |
| በአጠቃላይ አነጋገር የወላጆች ወደ ትምህርት ቤት መምጣት ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል | 3.640 | 0.555 | 3.602 | 0.563 | 0.697** |
| ወላጆች ልጆቻቸው ወደ ት/ቤት ሲገቡና ከት/ቤት ሲወጡ የትራፊክ አገልግሎት መስጠት አለባቸው | 2.782 | 1.046 | 2.886 | 0.939 | 1.077** |
| መምህራን የተማሪዎቻቸውን ችግሮችና ችሎታዎች በጥልቀት አጥንተው ከወላጆቻቸው ጋር ቢመካከሩ ጥሩ ነው | 3.578 | 1.095 | 3.602 | 0.649 | 0.366** |
| ወላጆች በት/ቤት ውስጥ በሚካሄደው የጥገና ሥራ ሊሣተፉ ይገባል | 3.085 | 0.732 | 3.261 | 0.692 | 2.528* |
| በቤት ውስጥ የልጆቻቸውን ትምህርት እንዴት ማገዝ እንዳለባቸው ት/ቤቶች ለወላጆች በቂ ግንዛቤ ማስጨበጥ አለባቸው | 3.526 | 0.671 | 3.441 | 0.669 | -1.308** |
| ወላጆች በት/ቤት እቅድ አወጣጥ ሥራ ላይ ውሣኔ በመስጠትና በማማከር መሣተፍ አለባቸው | 2.886 | 0.865 | 2.773 | 0.837 | -1.372** |
| ወላጆች በት/ቤት ውስጥ ለመማር ማስተማሩ ሂደት ድጋፍ የሚሠጥ ሥራ ቢሠሩ ይመረጣል:: | 3.171 | 0.683 | 3.104 | 0.749 | -0.951** |
| ርእሰ መምህራን የወላጆችን ክሂል፣ እውቀትና ልምድ ከመጠቀም ወደ ኋላ ማለት የለባቸውም | 3.123 | 0.733 | 3.152 | 0.687 | 0.411** |
| ስለተማሪዎች ትምህርት ሙሉውን ኃላፊነት መሸከም ያለባቸው መምህራን ናቸው | 1.957 | 0.917 | 1.953 | 0.861 | -0.055** |
| ት/ቤቶች ለተማሪዎች የሚሠጡትን ትምህርት በተመለከተ የወላጆችን ስምምነት ማግኘት አለባቸው | 2.455 | 0.957 | 2.370 | 0.831 | -0.977** |
| ተማሪዎች በት/ቤት ውስጥ ለሚያከናውኑት የተጓዳኝ ትምህርት ወላጆች ድጋፍ መስጠት አለባቸው | 3.341 | 0.715 | 3.119 | 0.690 | -3.255* |

* P<0.05 ** P>0.05 df = 420

በሌላ በኩል ደግሞ በትምህርት ቤት የወላጆችን ተሣትፎ በተመለከተ በወላጆችና በመምህራን መካከል የግምት ተዛምዶ በተመዘገበባቸው ጥያቄዎች የተገኙት አማካይ ውጤቶች በጣም ዝቅተኛ ሆነው መገኘታቸው በሠንጠረዥ 4 የተገኘውን ውጤት የሚያጠናክሩት ይመስላል:: ጥያቄ 9፣ 14፣ 19፣ 25፣ እና 28 ለአብነት ይጠቀሣሉ:: በነዚህ ጥያቄዎች ባ ላ ልዩነቱ አንዳለ ሆኖ፣ ለወላጆችም ሆነ ለመምህራን የተመዘገቡት አማካይ ውጤቶች ከሌሎች ጋር ሲነፃፀሩ በጣም ዝቅተኛ ናቸው:: በመሆኑም ባ ላ ልዩነት በተመዘገበባቸውም

ሆነ ካልተመዘገበባቸው ጥያቄዎች ለመረዳት እንደሚቻለው በትምህርት ቤት የወላጆች ተሣትፎ በራሣቸው በወላጆችም ሆነ፣ በመምህራን ብዙ ድጋፍ የተሰጠው አይመስልም፡፡

## የውጤት ማብራሪያ

በመግቢያው ላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው የዚህ ጥናት ዓላማ በወላጆችና በትምህርት ቤት መካከል ያለውን ግንኙነት መመርመር ነው፡፡ ይህንኑ በተመለከተ የተሰበሰቡት መረጃዎች ከተለያየ አቅጣጫ ተተንትነው የተለያዩ ውጤቶችን አስገኝተዋል፡፡ አስቀድሞ በጥቅል በተደረገው ትንተና ስለወላጆችና መምህራን ግንኙነትና ስለወላጆች የትምህርት ቤት ተሣትፎ የወላጆችና የመምህራን ግምት በስታትስቲክስ የጐላ ልዩነት (P>0.05) አላሳየም፡፡ ወላጆችና መምህራን በጋራ እንዲሠሩና በትምህርት ቤት የወላጆች ተሳትፎ እንዲኖር ሁለቱም ፍለጐት እንዳላቸው ውጤቱ አረጋግጧል፡፡ በተናጠልም ሲታይ በወላጆችና በመምህራን መካከል ስለሚኖር ግንኙነት በወላጆችና በመምህራን መካከል የግምት ልዩነቱ በስታትስቲክስ የጐላ አለመሆኑ (P>0.05) ተረጋግጧል፡፡ በሌላ በኩል ግን ፍላጐቱ ተግባራዊ ድጋፍ አላገኘም፡፡ በገላጭ መረጃ በተገኘው ውጤት ወላጆች ከመምህራን ጋር አብረው እየሰሩ ስለመሆናቸው የመመምህራንን ማረጋገጫ አላገኙም፡፡ አብሮ የመሥራት ፍላጐቱ ግን ጃሮሊሜክና ፎስተር (1997) እንደሚያስረዱት ከጋራ ግብ የመነጨ ማይሆን አይቀርም፡፡ በገላጭ መረጃው የተገኘው ውጤት እንደሚያሣየው በወላጆችና በመምህራን ግንኙነት አስፈላጊነት ዙሪያ ሁለቱም የጋራ ስምምነት አላቸው፡፡ ይህም ከጃሮሊሜክና ፎስተር (1997) ጥናት ጋር ተደጋጋፊነት አለው፡፡ በዘመኑ የወላጆችና የመምህራን ግንኙነት አስፈላጊነት እያደገ መምጣቱን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡

የመምህራንና የወላጆችን ግንኙነት በተመለከተ የሁለቱን ግምት ለመለካት ከቀረቡት ጥያቄዎች አንፃር ሁኔታው በዝርዝር ሲታይ የተገኘው ውጤት በጥቅል ከተገኘው ውጤት ጋር ሙሉ በሙሉ ተመሣሥሎ አላሳየም፡፡ ለዚሁ ተብለው በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ የወላጆችና የመምህራን ግምት በከፊል ስምምነትን ሲያሳይ፣ በከፊል ግን ልዩነትን አመላክቷል፡፡ ለዚህም በፖይኔና ሂንዲሰ (1986) ጥናት እንደተረጋገጠው፣ ዋናው ምክንያት የጋራ ግንዛቤ አለመኖር ሊሆን ይችላል፡፡

በትምህርት ቤት የወላጆችን ተሣትፎ በተመለከተ ግን የተገኘው ውጤት በጥቅል ትንተናውና የመምህራንና የወላጆችን ግንኙነት በተመለከተ ከተገኘው

ፈጽሞ የተለየ ነው። በትምህርት ቤት የወላጆች ተሣትፎ በራሣቸው በወላጆች የተሻለ ግምት ሲያሳይ በመምህራን ግን ዝቅተኛ ግምት ነው ያለው። ውጤቱም በጆንሰን (1995) ከተጠቀሰው የዋረን (1988) ከብላሴና ጆሴፍ ብላሴ (1997) ጥናቶች ጋር ይደጋገፋል። በተለይም መምህራን በትምህርት ቤት የወላጆች ተሣትፎ የተሻለ ውጤት ያመጣል ብለው ስለማያምኑ ከማንኛውም ወላጅ ጣልቃ ገብነት ነፃ ሆነው መሥራትን የሚመርጡ ስለመሆናቸው በነዚህ ጥናቶች ተረጋግጧል። በዚህም ጥናት መምህራን ለወላጆች ተሣትፎ ከፍተኛ ግምት ያለመስጠታቸው ምክንያት ከዚህ የተለየ ላይሆን ይችላል። ጥያቄ በጥያቄ ከተደረገው ትንተና የተገኘው ውጤት ደግሞ በትምህርት ቤት የወላጆችን ተሣትፎ በተመለከተ የራሣቸው የወላጆች ግምትም ቢሆን በብዙ ጥያቄዎች በጣም ዝቅተኛ ሆኖ ነው የተገኘው። በብላሴና ጆሴፍ ብላሴ (1997) እንደተረጋገጠው፣ ለዚህም ዋናው ምክንያት በራስ አለመተማመን ሊሆን ይችላል። ወላጆች ከመምህራን አንፃር ሲታይ ለራሣቸው ያነሰ ግምት ሊኖራቸው ስለሚችል በትምህርት ቤት ውጤት ያለው ተሣትፎ ሊኖራቸው እንደሚችል ላይቀበሉ ይችላሉ።

## ማጠቃለያ

በወላጆችና በትምህርት ቤቶች መካከል ያለውን ግንኙነት መመርመር የጥናቱ አቢይ ዓላማ ስለመሆኑ ቀደም ሲል ተጠቅሷል። ለዚህም ዓላማ ከግብ መድረስ በባህዳር ከተማ 12 አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ 211 መምህራንና በነዚሁ ትምህርት ቤቶች የምትማር/የሚማር አንድ ልጅ ያላቸው በ17ቱ ቀበሌዎች ኑዋሪ የሆኑ 211 መምህር ያልሆኑ ወላጆች በተጠኝነት ተመርጠዋል። እነዚሁ ተጠኝዎች የሞሉት መጣኝና ገላጭ መረጃ የያዘ መጠ ይቅ ለጥናቱ የሚፈለገውን መረጃ አስገኝቷል።

በመረጃው ትንተና መሠረትም አስቀድሞ ስለወላጆችና ስለመምህራን ግንኙነትና ስለወላጆች የትምህርት ቤት ተሣትፎ የወላጆችና የመምህራን ግምት በጥቅል በስታትስቲክስ ባ ላ ልዩነት አላሳየም ። በተናጠል ትንተናም በወላጆችና በመምህራን መካከል ስለሚኖር ግንኙነት የሁለቱ ግምት ከመጀመሪያው የተለየ አልሆነም። ሁለቱም ለግንኙነታቸው አዎንታዊ ግምት እንዳላቸው የትንተናው ውጤት አመላክቷል። ሆኖም ይህን ውጤት ገላጭ መረጃው በተወሰነ መልኩም ቢሆን ድጋፍ አልሰጠውም። ወላጆች ከመምህራን ጋር አብሮ ለመሥራት እምቢተኛ መሆናቸውን መምህራኑ አረጋግጠዋል። ከተግባራዊነቱ ውጭ ግን የወላጆችና የመምህራን ግንኙነት አስፈላጊ ስለመሆኑ ሁለቱም የሚጋሯቸው ነጥቦች ተመዝግበዋል።

በትምህርት ቤት የወላጆችን ተሣትፎ በተመለከተ ግን በወላጆችና በመምህራን መካከል በስታትስቲክስ ባ ላ የግምት ልዩነት ታይቷል:: በትምህርት ቤት የወላጆች ተሣትፎ በመምህራን ድጋፍ ሲያጣ፣ የወላጆች ግን አለው:: ጥያቄ በጥያቄ ከተደረገው ትንተና ለመረዳት እንደተቻለው አዎንታዊ የሚመስለው የወላጆች ግምትም ቢሆን በብዙ ጥያቄዎች ዝቅተኛ ውጤት የተመዘገበበት ስለሆነ ሙሉ በሙሉ ድጋፍ አላቸው ለማለት አይቻልም:: ቭህም ባ ራ መተ ዊ ትዛቤ አትሶ ል ወተሚል መተምተሚቨ ሊወስታ ቭኖላል::

በአጠቃላይ የወላጆችና የትምህርት ቤቶች ግንኙነት በፍላጐት ደረጃ በአብዛኛው አዎንታዊ በተግባር ግን አሉታዊ መሆኑን ጥናቱ አሣይቷል:: ስለዚህም በፍላጐት ብቻ የተወሰነውን ግንኙነት ወደተግባር ማሸጋገር እንዲቻል ከዚህ ቀጥሎ ያሉት አስተያየቶች ቀርበዋል::

- በብዙ አገሮች እንደሚታየው የወላጆችና የመምህራን የጋራ ማህበር ማቋቋም ግንኙነቱን ለማጠናከር አንድ መንገድ ሊሆን ይችላል፤
- መምህራን ስለተማሪዎቻቸው የትምህርት ቤት ውሎ ለወላጆቻቸው ሪፖርት የሚጽፉላቸውና በቤት አካባቢም ልጆቻቸውን በትምህርታቸው እንዴት ማገዝ እንዳለባቸው የሚጠቁሟቸው ቢሆን የሁለትዮሹ ግንኙነት ጠንካራ ይሆናል፤
- ወላጆችና መምህራን በዓመቱ መጀመሪያ የትምህርቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በጋራ የሚያቅዱበትና በዓመቱ መጨረሻ የዓመቱን ትምህርት በጋራ የሚገመግሙበት መንገድ ቢመቻች በወላጆችና በትምህርት ቤቶች መካከል ውጤታማ ግንኙነት መመሥረት ይቻላል፤
- በትምህርት ቤት ለሚደረገው የእለት ተእለት የመማር ማስተማር ክንውን የወላጆች ድርሻ በውል ተለይቶ ቢታወቅ፤ የወላጆች ትምህርት ቤትን የማገዝና የማጐልበት ፍላጐት ይጨምራል፤
- በፔምህርፔ ቤፔ ባወላ ኖት ተሳፔዐ አስወላ ቾ በተመለጸተ በዕውቀፔ በጎ ፔ ላቭ ባተመሰረተ ውቭቭፔ ጸመምህራት ጸወላ ኖ ር በማታረ ስለን ቃሚትቱ ባ ራ ትዛቤት ማሳተ ቢኖል ባ ርስ በርስ ተወላላ ትቱ ሊ ለብፔ ቭኖላል::

ዋቢዎች


ፔምህርፔ ሚኒስ ር:: (1994):: *ባፔምህርፔ አመራር አተረ ፔ፣ ባህብረተሰብ ተሳፔዐ ባዌቭ ትስ መመሪቨ*:: አ ስ አበባ፤ ፔ.መ.ማ.ማ.ታ.

Aggarwal, J.C. (1981). *Theory and Principles of Education: Philosophical and Sociological Bases of Education*. Dehhi: Vikas Publishing House Put Ltd.

Berres, Michaels S. (1996). *All Children, All Schools*. in Michael S. Berres et.al. (eds.). *Creating Tomorrow's Schools Today*: *Stores of inclusion change and Renewal*. Mew York: Teachers College Columbia University.

Blase, Jo and Joseph Blase. (1997). *The Fire is Back: Principles Sharing School Governance*. California: Crowin Press.

Brooksband, Kenneth and Keith Anderson (eds).. (1989*). Educational Administration.* London: Longman UK Limited.

Clark, Leonard H. and Irhing S. Starr. (1986). *Secondary and Middle School Teaching Methods*. New York: Macmillan Publishing Company.

Click, Phyllies. (1981). *Administration of Schools for Young Children*. New York: Oelmar Publishers Inc.

Crozier, Gill. (1996) *Black Parents and School Relationships: a Case Study*. **Educational Review**. 48/3: 253 - 267.

Eby, Judy W. (1997). *Reflective Planning, Teaching, and Evaluation for the Elementary School*. London: Printice - Hall, Inc.

Farrant, J.S. (1980). *Principles and Practice of Education*. London: Longman.

Good, Thomas L. and Jere E. Brophy. (1997). *Looking in Classrooms*. New York: Longman.

Habtamu Wondimu. (2001). *Ethiopia's Educational Policy Reform and the Trends on Human Resource Development*. **Ethiopian Journal of Development Research**. 23/1:1-35.

Jarolimek, John and Clifferd D.Foster, SR. (1997). *Teaching and Learning in the Elementary School.* United States of America: Printice Hall, Inc.

Johnson, Karen E. (1995) *Understanding Communication in Second Language Classrooms*. New York: Cambridge University Press.

Jowett, Sandra and Mary Baginsky. (1988). *Parents and Education: a Survey of their Involvement and Discussion of Some Issues*. **Educational Research**. 30/1:36-45.

McCombs, Barbara L. and Josue Whisler. (1997). *The Learner - Contered Classroom and School: Strategies for Increasing Student Motivation and Achievement*. Sanfrancisco: Jossey - Bass Publishers.

MOE. (1997). **Educational Journal**. Addis Ababa: Public Relations Services.

Olembo, Jolham Ombisi and John Cameron. (1986). *Practical Primary School Administration: for Students, Teachers and Schools*. London: Edward.

Payne, Monica A. and Jennifer O. Hinds. (1986). *Parent - Teacher Relationships: Perspectives from a developing Country*. **Educational Research**. 28/2:117 - 125.

Polloway, Edward A. and James R. Patton. (1997). *Strategies for Teaching Learners With Special Needs.* Tokyo: Prentice Hall, Inc.

Pumfrey, Peter D. (1986). *Paired Reading: Promise and Pitfalls*. **Educational Research**. 28/2: 89-93.

TGE. ($1994_a$). **Education and Training Policy**. Addis Ababa: EMPDA.

_____ ($1994_b$). **Educationale Sector Strategy**. Addis Ababa: EMPDA.

*Thomas, Gary (1987) Extra People in Primary Classroom*. ***Educational Research***. 29/3: 173-181.

Tizard, J., Schofield, W.N. and Hewison J. (1982). *Collaboration between Teachers and parents in Assisting Children's Reading*. **British Journal of Educational** *Psychology*. 52:1-15.

White, Kar R., Matthew J. Taylor, and Vanessa D. Moss. (1992). *Does Research Support Claimes the Benefits of Involving Parents in Early Intervention Programs*? 62/1: 91-125